**ለዘመናት ካሰቃየ የጤንነት ጉድለት ማረፍ፣** ዮሐ 5፡1-15

ዮሐ 5፡1-4፣ በኢየሩሳሌም የአይሁድ በዓል ስለ ነበረ ጌታ ኢየሱስም ወደዚያው ወጥቶ ነበር፡፡ በዓሉ ከአይሁድ በዓላት የትኛው እንደ ነበረ በግልጥ አልሰፈረም (ፋሲካ፣ በዓለ ሃምሳ፣…)

በኢየሩሳሌም ውስጥ ቤተሳይዳ በመባል የምትታወቅ አንዲት መጠመቂያ ነበረች፡፡ እግዚአብሔር ብዙዎችን ከተለያዩ በሽታዎችና የጤንነት ችግሮች ለመፈወስ ይጠቀምባት ስለ ነበር ወደዚያች መጠመቂያ የተለያየ በሽታና የአካል ጉዳት የነበረባቸው ብዙ ሰዎች ፈውስ ፍለጋ ይመጡ ነበር፡፡

ውሀው የመፈወስ ኃይል የሚኖረው፣ እግዚአብሔር በመልአኩ አማካይነት ሲያናውጠው ብቻ ነበር፡፡ የውሃው መናወጥ በውሃው ላይ የፈውስ ኃይል የመለቀቁ ምልክት ነበር፡፡ የእግዚአብሔርም ኃይል ህሙማንን ከማናቸውም መሽታዎች ይፈውስ/ያድን ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር መላዕክቱን ለሰው መልዕክት እንዲያመጡ ብቻ ሳይሆን ፈውስንም የሚያመጡ አድርጎ ይጠቀምባቸው ነበር፡፡ ሆኖም ውሃው ይናወጥ የነበረው አልፎ አልፎ ስለ ነበር ፈውስ ፍለጋ የመጡ ሰዎች የሚፈወሱት እንደመጡ ወዲያው ሳይሆን ውሃው በተንቀሳቀሰ ጊዜ ብቻ ነበር፤

ስለዚህ ወደ ውሃው ገብቶ ለመፈወስ የፈለገ ሁሉ የእግዚአብሔር የፈውስ ኃይል በውሃው ላይ በሚለቀቅበት ጊዜ አንድ ቀን እፈወሳለሁ በማለት በእምነት መጠባበቅ ነበረበት፡፡ ወደ ውሃው ቀድሞ የሚገባው አንድ ሰው ከሌሎች ህመምተኞች በፊት የውሃው መንቀሳቀስ የተመከለተና የተሻለ የመንቀሳቀስ አቅም፣ ወይም የሚረዳው ሰው ኖሮት ከሁሉም ቀደም ብሎ ወደ ውሃው መግባት ከቻለ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ አንዱ ፈጥኖ ሲድን ሌላው ዘግየት ብሎ ይጎበኝ ስለ ነበር እግዚአብሔር በራሱ ትክክለኛ ጊዜ የሁሉም ታማሚዎች ስራ እየሰራ እንደ ፈቃዱ በመፈወስ መልካም ያደርግ ነበር፡፡

በዚያ አንድ ለ38 ዓመታት ያህል በሽተኛ ሆኖ የኖረ ሰው በሕመሙ ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ አቅሙ በጣም የተዳከመ ስለነበረና የሚረዳውም ስላልነበረ ብዙ ጊዜ ቢጠባበቅም ለመግባት ሲሞክር በሌላው እየተቀደመ ሳይፈወስ ለብዙ ዘመናት ቆይቷል፡፡ ከእርሱ በኋላ ወደ ስፍራው የመጡት ሳይቀር በየተራ እየተፈወሱ ሲሄዱ የእርሱ ፈውስ ዘግይቶ ነበር፡፡

**ዮሐ 5፡5-6፣** ከላይ በተጠቀሰው የአይሁድ በዓል ቀን ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ መጣና ለብዙ ጊዜ በዚያ እንደ ነበረ አውቆ "ልትድን ተፈልጋለህን" አለው፡፡ ጌታ ፍላጎቱን የጠየቀበት ምክንያት ሰውየው እዚያ የቆየው ፈውስ ፍለጋ ቢሆንም፣ እዚያ የሚመጡ ሰዎች በሚሰጡት ምግብ/በልመና የሚኖር ስለሚሆንና ቢፈወስ የሚያገኘውን ምግብ ስለሚያጣ፣ ምርጫውን መወሰን ያለበት ራሱ ስለነበረ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ አንድ ችግር ከሰው ጋር ብዙ ጊዜ አብሮ ሲቆይ ሰውየው ተስፋ ከመቁረጡ የተነሳ የመፈወስ ፍላጎትም ሊያጣ ስለሚችል ነበር ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው መጀመሪያ ሲፈጥር ካልሆነ በስተቀር ያለ ባለ ጉዳዩ ፍላጎት/ፈቃድ ፈውስም ሆነ ማንኛውም ጸጋ

በግዴታ የማይሰጥ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡ ነገር ግን በጣም አልፎ አልፎ ቢሆንም ለእርሱ ስራ አመቺ እንደ ሚሆን ያወቀውን ሰው ፍላጎት ባይኖረውም መርጦት ኃላፊነት በመስጠት ሲጠቀምበት የሚታይ ጊዜ አለ፡፡

ሕመምተኛው ለጌታ የሰጠው መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡፡

**ዮሐ 5፥7-9፤** … “ጌታዬ፣ ውሃው በሚናወጥበት ጊዜ ወደ መጠመቂያዪቱ የሚያወርደኝ ሰው የለኝም፤ ለመግባትም ስሞክር ሌላው ይቀድመኛል” አለው።”

በመጨረሻም ሰውየው ጌታ ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ "አዎን መፈወስ እፈልጋለሁ" የሚል ቀጥተኛ መልስ ባይሆንም ወደ ውሃው ገብቼ እንዳልፈወስ እዚህ ለመፈወስ ከሚጠባበቁት ሁሉ ይልቅ አቅሜ ደከም ያለ በመሆኑ በሌሎቹ እቀደማለሁ፡፡ መዳን እፈልጋለሁ ግን የሚረዳኝም ሰው ስለ ሌለኝ ወደ ውሃው መግባት አልቻልኩም የሚል ይዘት ያለው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ሊያድነኝ ይችላል ብሎ ያስብ የነበረው በውሃው አማካይነት ብቻ እንደነበረና ከሁሉም የኃጢአት ውጤት የሚያድነው ጌታ ኢየሱስ እያናገረው መሆኑ አለማወቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የሚረዳኝ አጋዥ አጣሁ ባለበት በዚያው ሰዓት፣ ለካ አውነተኛውና ከማንም በላይ ሊረዳው የሚችለው ጌታው እዚያው አጠገቡ ቆሞ ነበር፡፡

ዛሬም የእያንዳንዳችን በሽታ/ችግር ምንም ያህል ከበድ ቢልብንና የሚረዳን ሰው ያጣን ቢሆንም ሁሉምን ቻዩ አምላካችን ሁሌ አጠገባችን ያለ መሆኑን በመረዳት ራሳችንን በእምነት በማበርታት ዓይኖቻችንን ሰው ላይ ሳይሆን ጌታችን ላይ ማድረግ ያሻል፡፡

- ጌታም ሰውየው መፈወስ የሚፈልግ መሆኑን ሲነግረው ተነስና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ስላለው ወዲያው ተፈውሶና በርትቶ ይሸከመው የነበረውን አልጋውን አንስቶ ተሸክሞ ሄደ፡፡ሕመምተኛው ባልጠበቀው ቀንና ሰዓት፣ ባልጠበቀው መንገድና ፍጥነት፣ ያድነኛል ብሎ ያላሰበው ጌታ ጤንነቱን ስላደሰለት በጣም ከመደሰቱ የተነሳ የፈወሰውን ጌታ አንተ ማነህ? ብሎ እንኳ ሳይጠይቀው አልጋውን ተሸክሞ ሄደ፡፡ ፈውሱ ለእርሱ ድንገተኛ፣ ለእግዚአብሔር ግን በታቀደው ጊዜ ነበር፡፡

**ከዚህ ክፍል የምንማረው ምንድነው?**

- ልክ እንደ ሰውየው ባይሆንም እያንዳንዳችን ከህይወታችን እንዲርቅ የምንፈልገው መለኮታዊ እርዳታ የምንሻበት ጉዳይ ይኖረናል፡፡ ስለዚህ አኔ ደካማ ነኝ ብንልና እነ እገሌና እገሊትም እየረዱኝ አይደለም በማለት ሰዎችን ብንወቅስ መለኮታዊ መፍትሄ አያስገኝልንም፡፡ ስለዚህ አማኞች ራሳቸው በጠበቁት ጊዜና መንገድ ከጌታ መፍትሄ ባያገኙም በራሱ ጊዜና መንገድ እንደ ሚደርስላቸው ማመን ይገባል፡፡

**ዮሐ 5፡14-15፣** ሕመምተኛው ሰው እንዲህ ዓይነት የከፋ የጤና ችግር እንዲደርስበት ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምስጢር፣ ራሱ የሰራው ኃጢአት ያስከተለበት ቅጣት መሆኑን ጌታ ገልጦታል እንጂ ባለጉዳዩ ስለ ሕመሙ መንስዔ ምንም ያለው ነገር አልነበረም፡፡

ለመፈወስ መጠመቂያው ጋ ደርሶ መቀመጥና ፈውስ መጠባበቅ ብቻ በቂ አልነበረም፡፡ ሕመምተኛው፣ እኔ ወሃው ውስጥ ልገባ ስል ሌሎች ቀድመውኝ ይገቡና ይፈወሳሉ በማለት ስለ ተናገረ፣ ውሃው በተናወጠ ጊዜ ቀድሞ መግባት የሚችለው መጠነኛ የመንቀሳቀስ አቅም ኖሮት ዝግጁና ንቁ ሆኖ የጠበቀ ከሆነ ነበር፣ ስለዚህ ማንኛውም ክርስቲያን የታመመ ከሆነ/በተለያየ የጠላት ውጊያ ውስጥ ካለ ብዙ ሳይቆይ ከጌታ ፈውስ/መፍትሔ ለማግኘት፡ -

**ሁሌ ዝግጁ በመሆን መጠበቅ ይጠይቅ ነበር**፡ - ፈጥኖ በመንቀሳቀስ ወደ መፈወሻው ለመግባት የሚያዘገዩ፣ የሚያደናቅፉ ነገሮችን፣ እነርሱ በነበሩበት ሁኔታ በሕመምተኛውና በውሃው መካከል የተቀመጡ ቁሳቁሶች፣ የደራረቡዋቸው ልብሶች…ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የአሁኑ ትውልድ ግን ፈውስ ወይም ለጉዳዩ መፍትሄ ለማግኘት በኩሬ ውሃ ውስጥ የሚገባ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚፈወስ በመሆኑ ቁሳቁሶችን ማስወገድ ሳይሆን፣ የፈጸሙት ኃጢአት መኖሩን ራስን በመመርመር ሲያገኙ በአግዚአብሔር ፊት መናዘዝና ኃጢአት ማድረግን በመተው ራስን ለፈውስ አመቻችቶ መጠበቅ ነው የሚያሻው፡፡

አንዳንድ ሰዎች በፈጸሙት ኃጢአት እውነተኛ ንስሃ በመግባት እልባት በመስጠት ከእግዚአብሔር መፍትሄ ከመቀበል ይልቅ ከችግራቸው ጋር አብረው ለመቆየት የሚመርጡ አሉ፡፡ (ለምሳሌ፡- የበደለን ሰው ይቅር ባለማለት፤ ቂም በመያዝ፣ በእልከኝነት…ወዘተ መቆየት የሚወዱ አሉ)፡፡ ያልታመመ ላለመታመም፣ የታመመም ለመፈወስ ኃጢአትን በመናዘዝ ከዚያም ኃጢአት ማድረግን በመተው ወደ እግዚአብሔር እየጸለዩ የእግዚአብሔርን ጉብኝት መጠባበቅ አስተዋይነት ነው፡፡

ሌላው አስፈላጊ ነገር **ንቁ ሆኖ በመገኘት መጠበቅ ነው**፡ - ይሄ በአእምሮ የተነቃቁ መሆንን ብቻ ሳይሆን ከአምላካችን የተሰጠ ኃላፊነትን በትጋት እየተወጡ፣ ማድረግ የጀመሩትን የአግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሥራ እየጀመሩ መተው ሳይሆን ሳያቋራርጡ በእምነት ጸንቶ በመቆም መጸለይና ማድረግ የሚገባውን የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ሁሉ አቅም በፈቀደ መጠን እያደረጉ በመቀጠል መጠበቅን የሚያመለክት ነው፡፡ ውሃው ምን ጊዜ እንደ ሚንቀሳቀስ የማይታወቅ እንደ ነበረው አሁንም የእግዚአብሔር መንፈስ ሁሌ አጠገባችን ቢሆንም የፈውስ ኃይል ምን ጊዜ እንደ ሚለቅልን ስለ ማይታወቅ ሁል ጊዜ ዝግጁና ንቁ ሆኖ በመገኘት መጠባበቅ ይጠይቃል፡፡ ማቴ 24፡42፣ ቆላ 4፡2፣

የዓለም አገራት መንግስታት ከዜጎቻቸው መካከል በሰሩት ጥፋት ተፈርዶባቸው በእስር ቤት ከተጣሉት ታራሚዎች ውስጥ በተለያዩ በዓላት ወቅት በእስር ቤት ቆይታቸው ወቅት መልካም ስነ-ምግባር ያሳዩትን የእስር/የቅጣት ጊዜያቸው ሳያልቅ በምህረት እንደሚፈቱት አምላካችንማ በዚህ ሁኔታ ተስተካክለው የሚያገኛቸውን ከምድር ነገስታት አብልጦ ፈጥኖ ምህረትና ፈውስ እንዴት አያደርግላቸቸውም?

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ኃጢአት ሲፈጽም የኃጢአቱ ዋጋ በተለያየ መንገድ እንደ ሚያስከፍለው/ተመጣጣኝ ቅጣት እንደ ሚቀጣው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡ ማቴ 5፡23-26፣ (18፡23-35)፣ ዮሐ 5፡6፣ 14፤

- እግዚአብሔር አንድ ክርስቲያን ሌላን ሰው በድሎ ከተበዳዩ ጋር በመነጋገር ይቅርታ ሳይጠይቅ/ተወያይቶ እልባት በመስጠት ጉዳዩን ሳይዘጋ በመቅረቱ ተበዳዩ በዳኛ ፊት ቢከሰው ይፈረድበትና የመጨረሻው ሳንቲም እስኪከፍል ከእስር ቤት አይወጣም ይላል፡፡ እግዚአብሔር ግን እስር ቤት ባያስገባም ጥፋተኛው እቤቱ እያለ ቀድሞ በነጻነት እየተንቀሳቀሰ በመስራት ያገኝ የነበረውን በረከት፣ ሰላምና ዕረፍት ጤንነቱን ለሚያውኩ በመፍቀድ ሊያሳጣው ይችላል፡፡
- አንድ ክርስቲያን ሌላን ሰው በድሎ በበደሉ ተጸጽቶ ተበዳዩን ይቅርታ እንዲያደርግለት በመጠየቁ ይቅርታ የተደረገለት ቢሆንም፣ እርሱ ራሱ ግን በሌላ ሰው ሲበደልና የእርሱ በዳይ ይቅርታ አድርግልኝ ብሎ ሲጠይቀው ይቅር ማለት እንቢ ካለ ቀድሞ ባጠፋው ጥፋት ተሰጥቶት የነበረው ይቅርታ ተሰርዞ በጥፋተኝነቱ የሚቀጣ መሆኑን ይናገራል፡፡

ደግሞም ሉቃ 4፡40፣ እንዲህ ይላል፡፡ "ፀሐይ መጥለቂያ ላይም፣ የተለያየ ሕመም ያደረባቸውን ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤ እርሱም በእያንዳንዳቸው ላይ እጁን ጭኖ ፈወሳቸው።"

እዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ ፊት የቀረቡ የተለያየ ሕመም ያደረባቸው ሰዎች ሁሉ እጁን በመጫን እንደ ፈወሳቸው ይናገራል፡፡ በቤተሳይዳ መጠመቂያ ፈውስ ይጠባበቁ ከነበሩት ሰዎች ውሃው ሲንቀሳቀስ የተወሰኑት ለምሳሌ 10ሩ ተከታትለው ቢገቡም የሚፈወሰው ከሁሉም ቀድሞ የገባው አንድ ሰው ብቻ ነበር፡፡ ዮሐ 5፡4፤ ጌታ ኢየሱስም እዚያ ከነበሩት ሕመምተኞች ሁሉ አንዱን ብቻ ፈውሶ ሌሎቹን ትቷቸው የሄደበት ምክንያት ልክ እንደ ተፈውሰው ሰው የቀሩትም በተለያየ ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር እየቀጣቸው እንደ ነበርና የቅጣታቸው ጊዜ ያላገባደዱ በመሆኑ ሳይፈውሳቸው እንደተዋቸው መረዳት ይቻላል፡፡ የተፈወሰውም ሰው ሊፈውሰው የራራለት በሰራው ኃጢአት ምክንያት በዚያ ለብዙ ዓመታት እየተቀጣ መቆየቱን ስላወቀ ነው፡፡ ዮሐ 5፡6፣

በመጠመቂያው አካባቢ ለመፈወስ ይጠባበቁ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ልዩነታቸው በኃጢአታቸው ምክንያት ለብዙ ወይም ለአጭር ጊዜ ታመው መቆየታቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመካከላቸው የታመሙ ጻድቃን ወይም እንደ ሽባው ሰው የቅጣት ጊዜያቸው የጨረሱ ቢኖሩ ኖሮ ጌታ ሳይፈውሳቸው ትቷቸው ባልሄደ ነበር፡፡ የፈወሰውን ሕመምተኛም ቢሆን እንዲህ ሲል አስጠንቅቆታል፤

ዮሐ 5፥14፣ "ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያን ሰው በቤተ መቅደስ አግኝቶ፣ "እነሆ፣ ተፈውሰሃል፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥራ፤ ያለዚያ ከዚህ የባሰ ይደርስብሃል" አለው።"

ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስን አምነው እንደ ተቀበሉ ለተወሰነ ጊዜ ኃጢአት ከማድረግ ስሚቆጠቡ የተለያየ ሕመም ወይም ውጊያ ሲደርስባቸው ጌታ ፈጥኖ እየደረሰ ማዳኑን ያሳያቸዋል፡፡ እያደር የተደረገላቸውን ውለታ በመዘንጋት ኃጢአት ማድረግ ሲደጋግሙ ግን ታመው ብዙ ቢጸልዩም ወይም የፈውስ አገልጋዮች ቢጸልዩላቸውም አይፈወሱም፡፡ ይህ የሚሆነው የአምላካችን እጅ ስላጠረች ሳይሆን ለውደፊቱ ከደረሰባቸው ችግር ተምረው

ኃጢአት ማድረግ እንዲተዉና ከዓለም ጋር እንዳይፈረድባቸው ነው፡፡ የፈውስ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ለነባር ክርስቲያኖች ከመጸለይ ይልቅ ለአዳዲስ ክርስቲያኖችና ላላመኑት ሰዎች ሲጸለይ የበለጠ መልካም ውጤት ይታያል የሚሉ አሉ፡፡ በመሆኑም የጌታን ፈውስ አንድ ሁለቴ ከቀመሱ በኋላ ደጋግሞ ኃጢአት ከማድረግ መቆጠብ የከፋ ጉዳት/ቅጣት በራስ ላይ ከማምጣት ሚያድን መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡

ሌላው በኃጢአቱ ምክንያት ሽባ ሆኖ በከባድ ሕመም ሲሰቃይ የነበረ ሰው በ ማርቆ 2፡3-11፣ የተጠቀሰው ሰው ተሸክመው ጌታ ካመጡት ሰዎች እምነት የተነሳ የኃጢአት ስርየትና ፈውስ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ስለሄደ በጽኑ እምነት እግዚአብሔር ፊት ከቀረቡ ለሰሩት ኃጢአት የተገባ ቅጣት ባይጨርሱም መፈወስ እንደ ሚቻል ያረጋግጣል፡፡

- በመጠመቂያው አጠገብ ብዙ ሰው ፈውስ ፍለጋ ቢሰበሰብም ውስጥ በመግባት ፈውስ ይቀበል የነበረው በተለያየ ጊዜ እንጂ ሁሉም በአንድ ቀን አልነበረም፡፡ አሁን የጸጋው ዘመን ስለሆነ በአንድ የጸሎት ጉባኤ በርከት ያሉ ሰዎች የሚፈወሱ ቢሆንም ፈውስ ፈልገው የመጡት ሁሉም በአንድ ቀን ስለ ማይፈወሱ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ቢደርስብን ተስፋ መቁረጥ አይገባም፡፡
- ሰውየው ከተፈወሰ በኋላ ያዳነው ማን እንደሆነ እንኳ ጠይቆ የማወቅ ጉዳይ ወደ ልቡ ሳይመጣለት ስለሄደ ማን ፈወሰህ ሲባል መልስ አጣ፡፡ ይህን ያህል ብዙ ዓመታት ካሰቃየው በሽታ ቢፈወስም ስለ ተዋለለት ውለታ ማመስገኑም አልተመዘገበም፡፡ በህይወታችን በሚሆነው ነገር ሁሉ ስለ ጌታ እርዳታ የማመስገን ልማድ ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ መዝ 107፡16-22፤
- ሽባው ሰው ምንም ያህል ፈውሱ ቢዘገይም የትም ሳይሄድ የቆየው በቤተሳይዳ እግዚአብሔር ፈውስ በሚሰጥበት ስፍራ ነበር፡፡

ይህ ሰው ፈውሱ ከመዘግየቱ የተነሳ ተሰላችቶ/ተቻኩሎ መፍትሔ ፍለጋ ወደ ሌሎች አማልክት/መፍትሔ አለን ባዮች ጋ ሄዶ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ብቻ የሚሰራው ኃያል ሥራ ማንም ስለ ማይሰራ (እግዚአብሔር ለአሳሪ አሳልፎ የሰጠውን ማንም ስለማይፈታ) ዕድሜ ልኩን በሽተኛ ሆኖ ይቀር ነበር፡፡

"ቤተሳይዳ/ቤተዛታ" የሚለው ቃል ትርጉሙ (በአራማይክ/በዕብራይስጥ)፡- ቤተስዳ፣) የምህረት ቤት ማለት ነው፡፡ *(አንዳንድ ትርጉሞች "በአራማይክ" ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ "በዕብራስጥ" ይላሉ፡፡)*

የእግዚአብሔር ቤት የምህረትና የትም የማይገኝ መፍትሄ የሚገኝበት ስፍራ ነው፡፡ ምናልባት በኃጢአት ምክንያት ነገሮቻችን ዘግይተውብን ከሆነ ኃጢአትን በመናዘዝ ከልብ የሆነ ንስሃ በመግባትና ኃጢአት ማድረግ ከመደጋገም በመራቅ ምህረት ተቀብለን ንጹህ እጆቻችንን ወደ እግዚአብሔር አንስተን ብንጸለይ የሚያስፈልገንን መፍትሔ ሁሉ ይሰጠናለል፡፡

እንዲወገድ (እንዲለቀቅ) የሚፈልጉት ነገር እጅ ሳይገባ ብዙ ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም ተስፋ ሳይቆርጡ በቤቱ ምህረቱን፣ ፈውስና ማዳኑን በእምነት እየተጠባበቁ ከቆዩ የጌታ ጉብኝት መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ነው፡፡